# ሳሙዔል ዓለማየሁ አራት ዓመት

በኢሕአፓ አባልነት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ በቆራጥነት ሲታገል የቆየው ጓድ ሳሙዔል ዓለማየሁ በሞት ከተለየን( ታህሳስ 1998) እነሆ አራት ዓመት አለፈ፡፡ ይህንኑ በመዘከር እህቱ ህና ዓለማየሁ የሚከተለውን የሀዘን እንጉርጉሮ አቅርባለች፡፡

## የሀዘን እንጉርጉሮ

አራት ዓመታት አስቆጠርን
ሞት ሳሙዔልን ከነጠቀን
የትካዜ የዋይ ዋይ ኩታ ካለበሰን፡፡
ባላሰብነው ጊዜና ሁኔታ
ተለየን ላይመለስ ላንጻፍታ፡፡
ሞትን አቸንፎ ላይመጣ ወደ እኛ
ገፁን ላናይ፤ ሳቅ ድምፁን ላንሰማ ሁለተኛ፡፡
መቁጠር ጊዜ ደቂቃ ሰዓቱን
ሆኗል ሞያ ተግባራችን
የቀን ተቀን ውሎአችን
ለምን? ለምን? ጥያቄአችን
አላገኘም መልስ እስካሁን
ዓላማ፤ተግባር፤ ቁምነገሩን እያሰብን
መኖሩን አለን በሐዘን ከስመን
ከቁጥር ጎድለን ተዛብተን ፡፡
ፋኖሳችን ጠፍቶ ተድላችን ተደምስሶ
አይናችን ሟሾ በለቅሶ
የማይጠፋ የማይቀንስ እሳት
ሆነብን የናፍቆቱ ግርፋት
የገና ደወል ቢያስተጋባ
ይጀምራል ልባችን ሊያነባ
ታህሳስ ወር ልዩ ለእኛ
ሰረቀን ሳሚን ከኛ
ፎቶህን ታቅፈን ትዝታህን ተጎናፅፈን
አራት ዓመታት አሳለፍን
የሳሙዔል ያለህ እያልን፡፡

ከእህቱ ከህና ዓለማየሁ